## <u>የአንበሳውን ዋሻ (ተስፋሁን ሞላ)</u>

የአንበሳውን ዋሻ ዝንጀሮ ሸንቶበት
ቦታ ማደሪያውን ሁሉን አበላሽቶት
ግማቱ ክርፋቱ አላስቀምጥ ብሎት
እየወጣ ሄደ እየለቀቀለት
ዝንጀሮ ዘለለ ለእሱ ቀን ወጣለት ፡፡
    የሚባላው ተበይ ሆነ ጊዜ ተቀይሮ
    የሚፈራው ፈሪ ሆነ እሳ ዘንድሮ
    በአንበሳው ጫንቃ ላይ ዘለለ ዝንጀሮ፡፡
የአንበሳውን ሱሪ ዝንጀሮ ቀዶበት
ጊዜ ጣለውና ደረሰበት ሽንፈት
ግርማና መጎሱ ክብሩ ተነክቶበት
እንዳይቀይር ሌላ ሁሉም ቀዳዳ ሆነበት
ገላውን የሚያሳይ ሁሉን እንደ ወንፊት
ገመናውን አይቶ ዓለምም ሳቀበት
እፍረት ያዘውና ያለቅሳል እንደ ሴት
አለ ተቀምጦ ተከናንቦ ቁጭትና ውርደት፡፡
    ሰፍቶ እንዳይታጠቅ ግራ ተጋብቶት
    መርፌውና ክሩ ከቤቱ ጠፍተውት
    አላውስም አለው ያ ክፉ ጎረቤት
    ጊዜ የማይቀየር የማያልፍ መስሎት፡፡
ከዚህ ሁሉ ነገር ከባአዳን ደጅ ከመጥናት
አሮጌውን ጥሎ አዲስ ቢተካበት
ይሻለው ነበረ ከድሪቶ ብዛት
እየደጋገመ መልሶ መላልሶ ከሚጠቀምበት፡፡
    ያ ክፉ ጎረቤት ማስተዋል ያቃተው
    ሱሪ አይለብስም ነበር እኛ እስከምናውቀው
    ጊዜ ሰጠውና አሳምሮ ለብሶ ተሸፈነ ገላው፡፡
አያውቅም ነበረ ሱሪ መታጠቅ
አሁን መልበስ ጀመር እኛ ስናወልቅ
በወገቡ አዘረ ዝናር ሙሉ ትጥቅ፡፡
    ቀሚስ ወለቀና ሱሪ ተለበሰ
    ሴት እና ወንዱን እያተራመሰ
    የአንበሳውን ቦታ ገብቶ አፈራረሰ
    ግመል መንዳት ቀርቶ እርሻውን አረሰ
    ያልደከመበትን የሰው ምርት አፈሰ
    ሱሪ ስለ አስታጠቀው ዜናዊ ለገሰ፡፡
ጊዜ ይረዝማል እንጂ መች ይቀርለታል
የታጠቀውን ሱሪ አውልቆ ይጥላል
አንበሳው ተነስቶ ብድሩን ይመልሳል
ይቅርና ሴቷን ወንዱን አበርከኳል
የሐበሻ ልጅ መች ተገዝቶ ያውቃል
እንኳንስ ለራሱ ለአፍሪቃም አኩርቷል፡፡
    ወልቃይት ጠገዴ ኧረ ምኑ ነካህ
    የአሳደከው ጥጃ በርግጫ ሲመታህ
    ማሰሪያውን ቀርጦ ሲያዞረው በአንገትህ
    አንገትከን ብትደፋ እንደ ኤሊ አርጎ አየሁ፡፡

እንግዲህስ ይብቃህ ከቤት መዋሉ ማደሩ
ዝምብለህ አትይ አረቦች መሬትክን ሲወሩ
ሁሉም ሰው ይነሳ ዘብ ይቁም ለሀገሩ
ክንድህን አሳይ ለእኒያ ለማይረቡ
አልሰማም ብለዋል ሁሌ ቢነገሩ።
መስከረም፤፳፫ቀን፡፪ሺ፲፫ /ዓም (30/09/2013)